በስመ አብ፤ ወወልድ፤ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

# የአስተዳደር ቦርድ የሥራ መግለጫ

የአስተዳደር ቦርድ በተደጋጋሚ በተደረገ ስብሰባ በተለያዩ ነጥቦች ላይ ተወያይቶ የረጅምና የአጭር ጊዜ እቅድ ከተለመ በኋላ ሊሰሩ ይገባቸዋል ተብለው የሚታሰቡትን በቅደም ተክተል እንደሚከተለው አቅርቧል።

፩ኛ፡- ወጣትና ታዳጊ ህጻናትን የሚያስተምር አስተማሪ መቅጠር።

ሀ. ልጆቻችን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት ታንጸው እንዲያድጉና የአገራቸውን ባህልና ወግ በሚገባቸው ቋንቋ ተምረው ኃይማኖታችንን ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲተላልፍ ለማድረግና የቤተክርስቲያናችን ተረካቢ እንዲሆኑ ለማዘጋጀት።

ለ. በቤተክርስቲያናችን ክርስትና ተነስተው፤ አድገው፤ በከፍተኛ ትምህርት ላይ የሚገኙና ትምህርታቸውን ጨርሰው በተለያየ የሥራ መስክ በመሰማራት ከቤተክርስቲያናችን የራቁ ወጣቶችን መመለስና ለታዳጊ ህጻናት አርአያ በመሆን ቤተክርስቲያናችንን እንዲያገለግሉ ማድረግ።

፪ኛ፡- ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎችን መስራት

- የቤተክርስቲያናችን ታዳጊ ህጻናት ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ የመማሪያ ክፍሎች ጥበት ስለተፈጠረ ይህን ችግር ለማቃለል ከምእመናን የተውጣጣ ኮሚቴ አቋቁሞ ሕዝቡንና የተለያዩ ተቋማትን በማስተባበር የገንዘብ እርዳታ ማስገኘት።


1106 N. Jupiter Rd. Garland, TX 75042
Tel. 972-487-0025 Fax: 972-487-1679 Email: Admin@stmichaeleoc.org

፫ኛ፡- የቤተክርስቲያናችን ህንጻ እደሳ ተደርጎለት ስለማያውቅ ጣራው የተለያየ ቦታ ላይ እያፈሰሰ ስለሆነ አስቸኳይ እድሳት ማድረግ።

- የተለያዩ ብቁ የሆኑ የጣራ ስራ (ሩፊንግ) ድርጅቶችን አወዳድሮ ስራው በጥራት እንዲሰራና የተሰራውንም ስራና ወጭ በዝርዝር ለምእመናኑ ማሳወቅ።

፬ኛ፡- የመኪና ማቆሚያ ሥፍራው (ፓርኪንግ ሎት) በወቅቱ ጥገና ተደርጎለት ስለማያውቅ እየፈራረሰ ስለሆነ ከአገልግሎት ውጭ ከመሆኑ በፊት እንዲጠገን ማድረግ።

፭ኛ፡- ማንኛውንም የቤተክርስቲያኑን የስራ እንቅስቃሴና የአስተዳደር ቦርዱ የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች ሁሉ በቤተክርስቲያኑ ድረገጽ (ዌብሳይት) ላይ በየወቅቱ ማውጣት።

፮ኛ፡- በአሁኑ ወቅት በአባላት የተጠቆሙ የሂሳብ አጣሪዎች በስራ ላይ ቢኖሩም ሥራቸውን እንደጨረሱ የ2009 ዓ/ምን አመታዊ ሂሳብ ሶስት የሂሳብ ቁጥጥር ድርጅቶችን በማወዳደር ሂሳቡ እንዲጣራ ተደርጎ ለአባላቱ የኦዲቱን ዘገባ ማቅረብ።

፯ኛ፡- ከ2010 ዓ/ም ጀምሮ በአመት አንድ ጊዜ በውጭ የሂሳብ ቁጥጥር (ኤክስተርናል ኦዲት) እየተደረገ በአመታዊ አጠቃላይ ስብሰባ ላይ ለአባላቱ የሂሳብ ዘገባ ማቅረብ። ከዚህም ሌላ የሂሳብ ባለሙያ የሆኑ ፈቃደኛ አባላትን አስተባብሮ የኦዲት ኮሚቴ በማቋቋም በቋሚነት በየሶስት ወሩ የውስጥ (ኢንተርናል) የሂሳብ ቁጥጥር እየተደረገ ለአባላቱ መግለጫ መስጠት።

፰ኛ፡- በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ያሉት ንኡሳን ኮሚቴዎች ለቤተክርስቲያኗ የሚያበረክቱትን ከፍተኛ አገልግሎት ግምት በመስጠት ለወደፊቱም ከነዚህ ኮሚቴዎች ጋር በመተባበርና ተቀራርቦ በመስራት የበለጠ ውጤት እንዲኖር ማድረግ።



1106 N. Jupiter Rd. Garland, TX 75042
Tel. 972-487-0025 Fax: 972-487-1679 Email: Admin@stmichaeleoc.org

፱ኛ፡- የምእመናኑን የወንጌል ትምህርት ፍልጎት ለማርካት የተለያዩ አስተማሪዎችን ከአካባቢውም ሆነ ከውጭ በመጋበዝ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን የጠለቀ ትምህርት እንዲማሩ ማድረግ።

፲ኛ፡- ቤተክርስቲያናችን የሚተዳደረው በአባላት ወርሃዊ ክፍያና ከምእመናን በሚለገሰው ስጦታ በመሆኑ የአስተዳደር ቦርዱ ማንኛውም ለቤተክርስቲያኑ እድገት ከምእመናን የሚቀርብ ጥያቄ ወይንም አስተያየት በመቀበል በግልጽ (ኦፕን ዶር) የሚያስተናግድ መሆኑን ይገልጻል።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች የአስተዳደር ቦርዱ በአጭር እና በረጅም ጊዜ መሥራት አለባቸው ብሎ ያቀረባቸው ሲሆኑ አባላቱ ለነዚህ ነጥቦች ማጠናከሪያም ሆነ ተጨማሪ አስተያየት ወይንም ሃሳብ ካላችሁ የተዘጋጀውን ፎርም ሞልታችሁ ለጽህፈት ቤቱ በማቅረብ በሃሳቡ ላይ ቦርዱ ተወያይቶ እንዳስፈላጊነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

የአስተዳደር ቦርዱ ይህን አላማ በሥራ ለመተግበር ሲያስብ የዚህ ቤተክርስቲያን ምእመናን ከዚህ በፊት ሲያደርጉት የነበረውን ቀናና ኃይማኖታዊ ድጋፋቸውን በተጠናከረ መልኩ እንደሚለግሱት በመተማመን ነው።

ሰው ያስባል እግዚአብሔር ይፈጽማል።

ወስብሃት ለእግዚአብሔር!!


1106 N. Jupiter Rd. Garland, TX 75042
Tel. 972-487-0025 Fax: 972-487-1679 Email: Admin@stmichaeleoc.org